

# ለክብራችሁ ዋጋ!



ለፍትህ፣ ላንድነት . . .ለነጻነት ዋጋ፣
ለሕዝብ ልዕልና . . .ላገር ክቡር ጸጋ፣
ኃያል ድምጻችሁን ባየር ስታመጥቁ፣
በትግል ጎዳና ተግታችሁ ስትልቁ፣
ለአካል፣ መንፈስ . .ጉዳት የተዳረጋችሁ፣
ውድ ሕይወታችሁን የተነጠቃችሁ፤
ደማችሁ ደመ-ከልብ ሆኖ እንዳልቀረ፣
የኢትዮጵያ መንፈስ በአብይ ተናገረ!





ከፋንታሁን . . .እስከ ሽብሬ ደሳለኝ፣
ከአሰፋ ማሩ . . . እስከ ታዳጊ ነብዩ፣
ከየኔሰው ገብሬ . . . እስከ አረጋዊ ገ/ዮሐንስ . . .፤
ከኦጋዴን . .እስከ ጋምቤላ፣ ከአዲስ አባ እስከ ሐረር፤
ከቤንጅ-ማጂ . . እስከ ዳውሮ፣ ከጅማ እስከ ባህር-ዳር፤
ከሁመራ . . እስከ ሞያሌ . .፣ ከወልድያ እስከ ጎንደር፤
ከአርሲ እስከ ወለጋ . .፣ ከአምቦ እስከ አፋር፤
ከኮንሶ እስከ ቢሾፍቱ . .፣ ከጋሞጎፋ እስከ ኢሉባቦር . . .፤





ከሰሜን፣ ደቡብ ጫፍ፣ ከምስራቅ፣ ከምዕራብ፣ በየማዕዘናቱ፣
ሃሳብ፣ ውጥናችሁ — ክቡር ዓላማችሁ የቀረ በከንቱ፣
ያልተወሳ ጎልቶ መልካሙ ስማችሁ፣
በ"ቤት ይቁጠር" ብሂል ጅምላ የተጠራችሁ፣
እናንት ሰማዕታት፣ የኢትዮጵያ ልጆች ሁላችሁ! ሁላችሁ . . !
ደማችሁ ደመ-ከልብ ሆኖ እንዳልቀረ፣
የኢትዮጵያ መንፈስ በአብይ ተናገረ!
ደግሞ ጊዜው ደርሶ ሃውልት እስከሚቆም . .
በናት ሃገር ምድር ለህያው ስራችሁ፣
እረፍት ይሁን አሁን — ለዘላለም ዓለም ለክቡር ነፍሳችሁ!!





ጌታቸው አበራ
መጋቢት 2010 ዓ/ም
(ኤፕሪል 2018)







---

(ፍትህ፣ እኩልነት፣ አንድነትና ነጻነት . . .በሀገራችን ምድር እንዲሰፍኑ፣ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በማሰማታቸው ሳቢያ፤ ለእንግልት፣ ለአካል ጉዳት፣ ለመንፈስ ስብራትና ለሞት የተዳረጉ ንጹሃን ዜጎቻችንን በማሰብ፣ አዲሱ ጠ/ሚ፣ ዶ/ር አብይ አህመድ በንግግራቸው ውስጥ በጠቀሷቸው በጎ ቃላት መነሻነት፣ ለህያው ጀግኖቻችን መልዕክቱን ለማስተላለፍ የተጫረች ግጥም ናት።)